በሶማሌ ክልልውስጥ የምንቀሳቀስ  የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ጋዜጣዊ ያቋም መግለጫ!

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ 6ኛው ሀገራዊ የምርጫ የክንውን ሂደት ሁሉን አቀፍ፣ ነፃ፣ ፍትሃዊ እና ሰላማዊ እንዲሆን እና በክልሉ ውስጥ የምንቀሳቀስ የተፎካካሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች በእኩልነት እና በነፃነት የመወዳደርና የመሳተፍ መብታቸውን ለማረጋገጥ ምቹ ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ፤ ማንኛውም የምርጫ እንቅስቃሴ በምርጫ መርሆች እና በሕግ እንዲመራ መንግሥት እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ተገቢውን የምራጫ ሥርዓት እንዲዘረጋ ገዢውን ፓርቲ ጨምሮ ሁሉም ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች በፈረሙት የጋራ ሰምምነት የቃልኪዳን ላይ እና በምርጫው ስነምግባር አዋጅ ማረጋገጡ ይታወሳል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከላይ በተጠቀሰው መርህ መሰረት የተፎካካሪ ፓርቲዎች ያላቸውን የተለያየ አመለካከት በሰላማዊ እና በሕጋዊ መንገድ ለመራጩ ሕዝብ በመግለጽ የሚያስተላልፉበትና ቅሰቀሳ በማድረግ በአንፃሩም መራጩ ሕዝብም በመረጃ ላይ በመመሰረት በነፃነት በመግለጽ ይበጀኛል ያለውን ወኪሎቹን የሚመርጥበት የምርጫ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ እያለ፣ በሶማሌ ክልል ውስጥ በተካሄደው  የመራጮች ምዝገባ ሂደት ችግር ያዘለ ከመሆኑም በላይ ከላይ ከተጠቀሰው ሕግና የምርጫ ሥርዓት የጣሰ ከመሆኑ በላይ የምርጫውን ምንነት ትርጉም የሚያሳጣ ለአንድ ወገን ያዳላ በመሆኑ ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ከዚህ በፊት ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ያቀረብናቸው ቅሬታዎች ሊፈቱ ባለመቻላቸው እና የምርጫውን ሂደት ተዓማኒነት የሚሳጣ ስለሆነ የሚከተሉትን የጋራ አቋም መግለጫ አውጥተናል።

1.  ከዚህ በፊት ተሰርቆ የነበረው የምርጫ ቁሳቁስ በአዲስ እንዲተካ የጠየቅን ቢሆንም አሁን ግን ቀድሞ ተዘርፎ በነበረው ካርድ ወደ ምርጫ በመገባቱ ምርጫው ተዓማኒነት አይኖረውም። በተጨማሪም የምርጫ ጣቢያ ያልተቋቋመባቸው አካበቢዎች ምርጫ ጣቢያ እንዲቋቋም ጠይቀን የነበረ ቢሆንም ከብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የተሰጠው ምላሽ አጥጋቢ ባለ መሆኑ፤

2.  በየደረጃው መዋቀር የነበረበት የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ መዋቅር ከመንግሥት መዋቅር ጋር የተዋሀደ መበሆኑ እና እነዚህ የምርጫ አስፈፃሚዎች የምርጫ ቁሳቁስ አዘርፈው በሕግ መጠየቅ ሲገባቸው አሁንም ምንም ዓይነት ማሻሻያ ሳይደረግ በዛው መንገድ በመቀጠሉ የምርጫውን ፍትሀዊነት እና ተዓማኒነት የሚያሳጣው በመሆኑ፤

3.  ከብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የቀረቡ የምርጫ ቁሳቁስ ድልድል ሂደት፣ የምርጫ አስፈፃሚዎች ምልመላና ሥልጠና ሂደት፣ ስለመራጮች ምዝገባ ሂደትና የግዜ ሰሌዳ አለማስቀመጥ እና አሁንም በዛው ሂደት የቀጠለ በመሆኑ፤

4.  ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በኩል የሠለጠኑ ሠልጣኞች ሳያውቁ የምርጫ ቁሳቁስና ሰነድ በወረዳና በቀበሌ የመንግሥት መዋቅር ሠራተኞች እጅ በመግባቱ ይህም ለገዢው ፓርቲ ብቻ የሚያገለግል በመሆኑ እና አሁንም በዛው መንገድ በመቀጠሉ፤

5.  ባለው የመረጃ ክፍተት ምክንያት ለተፎካካሪ ፓርቲዎች ለእያንዳንዱ የምርጫ ክልል ምን ያህል የመራጮች ካርድ እንደመጣ ግልጽ አለመሆን ምክንያቱም ቁሳቁሱን እያጓጓዘ ያለው የወረዳና የቀበሌ መስተዳድር  መዋቅር በመሆኑ በመርሁ መሰረት ለአንድ ዕጩ በየምርጫ ክልሉ የራሱን ታዛቢ እንዲኖር ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከ15 ቀን በፊት ማሳወቅ አለበት የሚለው መርህ በመጣስ የምርጫውን ነፃ እና ፍትሀዊነት  ጥያቄ ውስጥ ያስገባ በመሆኑ መስከረም 20 ቀን 2014 ዓ.ም ከሚካሄደው ምርጫ ራሳችንን  ያገለልን መሆናችንን  እናሳውቃለን ።

የውሳኔው አካላት

1.  የነፃነትና የእኩልነት ፓርቲ (ነዕፓ)

2. የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ ፓርቲ (ኢዜማ)

መስከረም 9 ቀን 2014 ዓ.ም

ጅግጅጋ ኢትዮጵያ